**ለትርጉም**
**Lancet Global Health**

## ያልታተመ ረቂቅ የፅሁፍ ማጠቃለያ

**ዳራ** የኢንፍሉዌንዛ ወረርሽኝ እንቅስቃሴን ለመግለጽ አገር ተኮር የክትትል መረጃዎችን መጠቀም የኢንፍሉዌንዛ ክትባት የሚሰጥበትን ጊዜ በተመለከተ ለሚደረጉ ውሳኔዎች ሊረዳ ይችላል። ብሔራዊ የክትባት ስትራቴጂዎችን ለመወሰን ወቅታዊ የኢንፍሉዌንዛ ወረርሽኝ የሚከሰትበትን ጊዜ ለመለየት ከአፍሪካ ሀገራት የተገኙ የክትትል መረጃዎችን ተንትነናል።

**የጥናት ዘዴዎች** ለዓለም አቀፉ የኢንፍሉዌንዛ ክትትልና ምላሽ (GISRS) አውታረመረብ ሪፖርት ካደረጉ አገራት ከ2010–2019 የተሰበሰበ ከ3–10 ዓመታት የሚሆን በይፋ የሚገኝ የ sentinel መረጃን ተጠቅመናል። ለኢንፍሉዌንዛ ቫይረስ ፖዘቲቭ የሆኑ ናሙናዎች ድርሻ የ3 ሳምንታት ተንቀሳቃሽ አዎንታዊነት ያሰላን ሲሆን የወረርሽኙን ጊዜ ጥርቅም አማካይ ዘዴ በመጠቀም ገምግመናል። የእያንዳንዱ ወረርሽኝ መጀመሪያ እና ማብቂያ ምጥነት በቅደም ተከተል ለ ≥3 ተከታታይ ሳምንታት ከዓመታዊው አማካይ በላይ ወይም ከዚያ በታች በሚሆንበት ጊዜ የመጀመሪያው ሳምንት የሚል ፍቺ ተሰጥቶታል። አገሮችን በአምስት የወረርሽኝ ቅጦችን መድበናል፡ ሰሜናዊ ንፍቀ ክበብ [Northern Hemisphere (NH)] ወረርሽኝ ከኦክቶበር-ማርች የሚከሰት፣ Southern Hemisphere [ደቡባዊ ንፍቀ ክበብ (SH)] ከኤፕሪል እስከ ሴፕቴምበር የሚከሰት፣ በዋናነት ሰሜናዊ ንፍቀ ክበብ ሆኖ በደቡባዊ ንፍቀ ክበብ ወራቶች ውስጥ የተወሰነ የወረርሽኝ እንቅስቃሴ ያለው፣ በዋናነት ደቡባዊ ንፍቀ ክበብ ሆኖ በሰሜናዊ ንፍቀ ክበብ ወራቶች ውስጥ የተወሰነ የወረርሽኝ እንቅስቃሴ ያለው፣ እና ምንም የሚስተዋል የሰሜናዊ ንፍቀ ክበብ ወይም የደቡባዊ ንፍቀ ክበብ የበላይነት ሳይኖር (ግልጽ አካሄድ የሌለው) ዓመቱን ሙሉ የኢንፍሉዌንዛ ስርጭት የሚከሰትበት።

**ግኝቶች** ለFluNet መረጃ ከሚያቀርቡት 34 አገሮች መካከል 25ቱ ቢያንስ የ3 ዓመት መረጃ የነበራቸው ሲሆን ይህም 46% የሚሆኑትን የአፍሪካ አገራት እና 89% የሚሆነውን የአፍሪካ ህዝብ ይወክላል። የጥናቱ አገራት በድምሩ ለ 503,609 ናሙናዎች (መካከለኛ 12971 [IQR 9607     20960] በአገር-ዓመት) የRT-PCR የመተንፈሻ አካላት ቫይረስ ውጤቶችን ሪፖርት አድርገዋል ከእነዚህ ውስጥ 74001 (15%፥ መካከለኛ 2078 [IQR 1087 – 3008] በአገር-ዓመት) ለኢንፍሉዌንዛ ቫይረሶች ፖዘቲቭ ውጤት ነበራቸው። በ236 የአገር-ዓመታት መረጃ 248 ወረርሽኞች ተከስተዋል (መካከለኛ፡ 10፤ [ክልል: ከ7-10] በአገር)። ስድስቱ (24%) የሰሜናዊ ንፍቀ ክበብ ቅጥ ነበራቸው (አልጄሪያ፣ ቡርኪና ፋሶ፣ ግብፅ፣ ኒጀር፣ ሞሮኮ እና ቱኒዚያ)። ስምንቱ (32%) ከተወሰኑ የደቡባዊ ንፍቀ ክበብ ወረርሽኞች ጋር በዋነኝነት የሰሜናዊ ንፍቀ ክበብ ቅጥ ነበራቸው (ካሜሩን፣ ኢትዮጵያ፣ ማሊ፣ ሞዛምቢክ፣ ናይጄሪያ፣ ሴኔጋል፣ ታንዛኒያ እና ቶጎ)። ሶስቱ (12%) ከተወሰኑ የሰሜናዊ ንፍቀ ክበብ ወረርሽኞች ጋር በዋነኝነት የደቡባዊ ንፍቀ ክበብ ቅጥ ነበራቸው (ጋና፣ ኬንያ እና ኡጋንዳ)። ሶስቱ (12%) የደቡባዊ ንፍቀ ክበብ ቅጥ ነበራቸው (የመካከለኛው አፍሪካ ሪፐብሊክ፣ ደቡብ አፍሪካ እና ዛምቢያ)። አምስቱ (20%) ግልጽ የሆነ ቅጥ አልነበራቸውም (ኮት ዲቩዋር፣ ኮንጎ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ፣ ማዳጋስካር፣ ሞሪሺየስ እና ሩዋንዳ)።

**ትርጓሜ** አብዛኛዎቹ አገሮች የወቅታዊ እና ወቅታዊ ያልሆነ የኢንፍሉዌንዛ እንቅስቃሴን ለባለስልጣናት ለማሳወቅ፣ የክትባት ጊዜን ለመምራት፣ እና ወቅታዊ ጣልቃ ገብ እርምጃዎችን ለማስተዋወቅ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ተለይተው የሚታወቁ የኢንፍሉዌንዛ ወረርሽኝ ጊዜያት ነበሯቸው።

**ለትርጉም**
**Lancet Global Health**

**የገንዘብ ድጋፍ** የለም